# <u>አገር ከሃዲዎች</u>
# <u>የጠላት አጋር ባንዳዎች</u>

ከቀመሩ ደሳለኝ

ኢትዮጵያን የተፈታተኗት፣ የተዳፈሯት፣ የተዋጓትና የተጠቃችው በውጭ ጠላት ብቻ ሳይሆን በውስጥዋ በበቀሉ የእኔ ናቸው በአለቻቸው አገር ከሃዲዎች ፣ የጠላት አጋር ባንዳዎች ጭምር ነው። ባንዳዎች ከጠላት ጋር ተባብረው ወግተዋታል፣ አስወግተዋታል፣ አቁስለዋታል፣ አስጠቅተዋታል ብዙ ጉዳትን አድርሰውባታል። አገርን አስወርሮ ጠላትን በመርዳት ለአገር ነፀናት በቁርጠኝነት የቆሙትን የክፉ ቀን ልጆችዋን ደም አፍሰዋል። ለከፍተኛ የመራራና የተራዘመ ችግርና ስቃይ በአገርና በወገን ላይ እንድፈጸም በማድረግ በታሪካችን ውስጥ ክፉኛ ጥቁር ነጥብ በመጣል የተመዘገበና አሁንም ብዙ ሸንኮፉ ጨርሶ ያልተነቀለ፣ ቅሪት አካል አገራችንን በእጅጉ እየጎዱ ይገኛሉ ።

ኢትዮጵያ የተከበረች ብርቱና ጠንካራ የነፃነት አፍቃሪና ጠባቂ ጥንታዊት አገርነቷ በስፋት የታወቀ ምሳሌነት አለው። ኢትዮጵያ ታሪኳን የሚጽፍላት፣ የሚናገሩላት፣ የሚያወሱላት አያሌዎች ናቸው። እጅግ ብዙ ታላላቅ ፈላስፋዎች፣ ተመራማሪ ሳይንቲስቶች፣ የሃይማኖት መሪዎች፣ ታሪክ ጸሐፊዎች፥ተራኪዎችና ፣ ትርጉም ጸሐፊዎች በዓለም ዙሪያ ያሉና የሚገኙ የሰበዓዊ መብት ተቆርቋሪዎች፣ የግብረገብነትና የሥነ-ምግባር አዋቂውች፣ አገር፣ ሰውና ሕግን አፍቃሪና አክብሮት፣ፈሪሃ እግዚአብሔር ያላቸው ሁሉ ናቸው።

ከነዚህ ከኢትዮጵያ አንኳር አንኳር የታሪክ መጻሕፍት ውስጥ በቀደምት ለመጥቀስና ለአንባቢያን ላሳስብና ላካፍል የምወደው ኅብረተሰብ በአገር ፍቅርና ነፃነት ላይ ያለውን ባሕሪ የሚገልጽትን የጦር ወቅት መጸሐፍቶች ነው። እነዚህ ታላላቅ የኢትዮጵያና የሕዝብ ታሪኳን ቁልጭ አድርገው የሚያሳዩና የሚገልጹ መጸሐፍት ውስጥ በዋናነት የሚጠቀሱት አረመኔው ጣሊያን በኢትዮጵያ ላይ ያደረገውን የወረራ ሙከራ ጦርነት ጊዜና ሁኔታን ያካተቱ ናቸው።
1-ቀይ አንበሳ በኮ/ል አልኽንድሮ ዴል ባየ የኩባ ዜጋ( 1928 )
2-የሃበሻ ጀብዱ በአደልፍ ፓርለሳክ የቼክ ዜጋ (1948፣ 1989)ከኢትዮጵያ አርበኛች ጋር አብረው በወዳጅነት የተሰለፉ ለእኛ ለጥቁሮች ያዘኑና የረዱን ፣ የተካፈሉና የተዋጉ በዓይነ-ሕሊና ያዩና የታዘቡ የጻፍት የኛ የኢትዮጵያኖች ታሪክ ነው።

የጀግና አርበኞች አኩሪ ገድሎችውን የሚገልጽ በታሪካችን ቀዳሚ ምእራፍ የያዘ ኢትዮጵያን የሚያኮሩ፣ እንደአገር አስከብሮና የታፈረች ነፃ ያደርጓትን የትግል አሰላለፍና በጦር ስልት ሜዳ ጀብዷቸውን፣ ቆራጥነትና ፅናታቸውን ያብራሩና የሚገልጽ ናቸው።

ኢትዮጵያ በአረመኔው ጣሊያን የተሞከረባትን ወረራ ድል ነስታ በነፃነት ተከብራና የታፈረች ሆና የኖረችው በጀግኖች ኢትዮጵያ ልጆች በማይበገር ኃይልና ድፍረት አገር የመጠበቅ እምነትና ብልህነት ነው ። ከማንምና ከምንም በላይ ለአገር በሚሰጡት ኃላፊነትና ግደታ ራስን በመሰዋዕትነት አሳልፎ በማስቀደም አጥንትና ደማቸውን በመከፈል ነበር። አገርን እንደ አገር ለዚህ ትውልድ ያደረሷትን የጀግኖች ልጆችዋን መልካም ታሪክ ገጽታን የያዙ መጽሐፍት ሲሆኑ በአንጻሩ ደግሞ በአገርና ወገን ወንድም-እህት ላይ ትልቅ ክህደትን ፣ የጠላት አጋር ባንዳ በመሆን አገርን አሳልፎ ለወራሪው በጥቅም፣ ተገዥ በህሪና ተላላነት የጎዷትን የሕዝብ ክፍሎች ጭምር ነው።

ይህ የአለፈው ትውልድ መልካም ታሪክ የዛሬውና የነገው ትውልድ የመኖር ተምሰሌት ሕያው የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪኩ የሚኮራበትና የሚመካበት የምንጊዜም ሃብት ነው፤ ሊያውቀው፣ ይረዳውና ሊገነዘበው እንድችል እነዚህ መጸሕፍት መነበብ መጠናትም አለባቸው።

እነዚህ በኢትዮጵያ ምድር ያልተወለዱ ዜግነቱ የሌላቸው እኛን ኢትዮጵያዊያንን ሳይሆኑ ከእኛ አርበኞች ጋር ተሰልፈው መስዋእትነትን የከፈሉ ፣ የጣሊያን ወረራንና አረመኔዊ ተግባሩን የተቃወሙና ያወገዙ የኢትዮጵያ ወዳጆች ናቸው ። በቆራጥነት ከቆመው የኢትዮጵያ ሕዝብ ወገን ሆነው ጀግናው ኢትዮጵያዊ የሚያደርገውን ሁሉ በግንባር አብረው የፈጸሙ፣ ተዋግተውና አዋግተው፣ ቆስለውና ደምተው፣ ተርበውና ተጠምተው፣ አቅበትና ቁልቁለቱን፣ ጫካውና በረሀውን፣ ወጥተውና ወርደው በመሸጋገር በአረመኔው ጣሊያን ከአይሮፕላን የሚወርደውን ቦምብና የመርዝ ጭስ፣ የታንክና የመድፍ፣ እንድሁም የባንዳውን ሸፍጥና ሌብነት ያዩ የሞት ሽረትን ጽዋ የቀመሱና የተቀበሉ ናቸው። ዜጋና ሳይወለዱባት ለኢትዮጵያና ሕዝብ ፍቅርና አክብሮት፣ ስበዓዊነት በማሳየት፣ ለአገሩ ነፃነትና ማንነት ከሚታገለው ጀግና ኢትዮጵያዊ ጎን በአካል ተገኝተው አስፈላጊውን ያደረጉና የተመለከቱ የእውነት አጋሮች ነበሩ።

እነዚህ ታሪክ ጸሃፊዎች የኢትዮጵያ አጋዥና አጋር የነበሩት በአረመኔው ጣሊያን የግፍ ወረራ ጊዜና ከሃዲ ባንዳዎች የጠላት አጋር ሆነው አገርን በሸጡበትና ወገንን በወጉበት ጊዜ እውነቱን የተገነዘቡበትና የተመለከቱበት ወቅት ነበር።
ኢትዮጵያዊ የሚያደርገውን መስዋእትነት ለኢትዮጵያ የከፈሉና በእውነት ለሰው ልጅ በሃቅ የቆሙ የእውነት ሰዎች ናቸው። የኢትዮጵያ ሕዝብን ታሪክ በጥንቃቄ አይተውና በደንብ አገናዝበው ፣ ገምግመው፣ ታዝበውና አነጻጽረው በመጻፍ ለባለታሪኮቹ ለኛ ኢትዮጵያዊያንና ለጠላቶች፣ ለባንዳ ከሃዲዎች ጭምር ማንነትና ምንነት የሚገልጽ ተግባርን በጥሩ ሁኔታ ቁልጭ አድርገው መዝግበው ጽፈውታል።

ይህን መሰል ድንቅ የነፃነት ትግል፣ ማነው ኢትዮጵያዊ ታሪካችንን በግልጽና በጉልህ የቀደምት ትውልዶችን ጀግንነትና የአገር ጥበቃ ኃላፊነት ፍጹም ኢትዮጵያዊነትን በሚያመለክት ገንዛቤ ጽፈው ስላቆዩን እጅግ የሚመሰገኑና ታልቅ አክብሮት የሚሰጣቸው የታሪካችን አካል ዴራሴውች ናቸው።

ለኩባው ዜጋ ኮ/ል አልኸንድሮ ዴል ባዬ ና ለቼኩ ዜጋ አዶልፍ ፓርለርክ እጅግ በጣም የከበረ አድናቆት፣ አክብሮቴንና ፍቅሬን ጥልቅ በሆነ ልባዊ ምስጋና እየገለጽ ፤ ለዚህ ለተቀደሰ መልካምና በጎ ተግባራቸው እግዚአብሔር ይባርካቸው፣ ያከብራቸው፣ የዘለዓለም ሕይወት ለቤተሰቦቻቸውና ለዘመዶቻቸው ሁሉ ይለግስና ያበለጽግ ዘንድ የዘወትር ጸሎቴና ምኞቴ ነው።እንድሁም በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ሕያው የሆነ ምንጊዜም የታሪክ ስፍራ ከትውልድ ትውልድ የክብር ትውስት ምስጋናና ፍጽም የክብር ታሪካዊ መዘክር እንድሰጣቸው በኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ፣ በሰንደቅ ዓላማው ለሚያምን ሁሉ በክብር እጠይቃለሁ።

ወራሪው የጣሊያን መንግሥትይህን እውነትን በመካድና በመሸፈን በነዚህ ሁለት የእኛ ረዳት ወገኖች ላይ እውነትና ትክክለኛ መልካም ስራን በመስራትና በመጻፋቸው ሃቅ የጎደለው አሉባልታና ውሸት በመፍጠር ነጭን የከዱ ፣ ከጥቁር ጎን የተሰለፉ ፣ የወጉን ፣ መጥፎና አረመኔዊ ታርኬን በማውገዝና በማጋለጽ የጻፉብኝ በማለት የማስተባበል ተቃውም እንዳሰማ፣እንደተናገረና እንደጻፈ ይታወቃል። እንድሁም ባንዳው ኢትዮጵያዊ ነኝ ባይ ይህን ሃቅ የሚክዱ የዘመኑ ወያኔዎች የባንዳነት ታሪካቸውን በመካድ ፣ በውሸትና በሃሰት ያስተባብላሉ ፣ አይቅቀበሉትም። ሃቁ ግን ባንዳዎች ከጠላት ጋር ተባብረው ወገንን የወጉበትና የአገርን ነፃነት የተቃወሙበት በእውነት የኢትዮጵያና የሕዝቧ ታሪክ ነው።

ለእኛ ኢትዮጵያዊያን በነዚ መጸሐፍት የተገለጸው እውነትና ሃቅ ታሪካችንን በጉልህ የሚያስይ የነበረና ያለ ስለሆነ በጽኑ መታየት አለበት።ይህ የአንድ አገር ኅብረተሰብ ታሪክ ለአገሩ የሚያሳየው ፍቅርና የሚያደርገውን የነፃነት አለኝታና ክብር ፣ ማንና ምንነትን የሚያስረዳ የኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ፍጹም ታሪክ ነው። ከዚህ ፍሬ ታሪኩ በመነሳት ማንም ኢትዮጵያዊ አገሩን ያውቅ፣ ማንነቱን ይረዳ፣ይገነዘብ፣ በአገሩ ባለቤትነት ይኮራና ይጠብቃት፣የአገር ፍቅር ይኖረው፣ ራሱን እንደ ኢትዮጵያዊነት ያስተምርና ይቀርጽ ዘንድ እነዚህን መጸሐፎቶች ማንበብና ማጥናትም ይኖርበታል።

ኢትዮጵያን ምንጊዜም እግዚአብሔር የሚታደጋት አገር ስለሆነች የሚወዳት፣ የሚያከብራትና የሚጠብቃት ትውልድና የሚረዷት ሰዎችን ይፈጥራል፣ ይልካል። እነዚህ ሁለት መጸሕፍት በተለያዩ የውጭ አገረ ዜጎች በስፓኒሽና በቼክ ቋንቋ የተጻፉ ናቸው።እነዚህን ቋንቋዎች በተማሩና በተረዱ የኢትዮጵያ ልጆች ሕዝብ የአገሩን ታሪክ በቋንቋው ያነበውና ያውቀው ይችል በማሰብ ወደ አገራቸው ቋንቋ አማርኛ ተርጉመው ለሕዝብ እንድደርስና እንድነበብ አብቅተዋል።የአገርና ወገንን አኩሪ ታሪክ፣ መልካም ተግባርና የጀግንነት፣ ጀብዱ ሥራቸውና ኃላፊነትን የጠበቀ የኢትዮጵያን አርበኞች ታሪክ የሚያወሳ፣ ማነው ኢትዮጵያዊ ለአገሩ የሞተ የሚገልጹና የሚያስረዱ መጸሕፍትን ተርጉሞ ማቅረብ በራሱ ትልቅ ሥራና ኃላፊነት ነው።ለአገርና ለሕዝብ አክብሮትና ፍቅር የኅብረተስ አካል ኃላፊነትና ግደታንም መወጣት ነው ።ይህን የታሪክ ግደታ የአገር ፍቅርና አክብሮት የተወጡና የአገራችንን ታሪክ አንብበን እንድንገነዘብ የረዱን ከየቋንቋው ተርጉመው ለአቀረቡልን ለአስተማሩን ባለሙያዎች ፤
1-ዶ/ር ተስፋዬ መኮነን ባይለየኝ (ቀይ አንበሳ፣ ከስፓኒሽ ቋንቋ) ሲሆን
2-አቶ ተጫኔ ጆበሬ መኮነን (የሃበሻ ጀብዱ ፣ ከቼክ ቋንቋ) ውድ የኢትዮጵያ ልጆች ምስጋና ይድረሳቸው። ተምረው ያስተማሩ የወገን ተቆርቋሪ ትውልድ አክባሪ ሥራቸውን ከልብ በማድነቅ አክብሮትና ፍቅሬን እገልጻለሁ። በአውነት የሚደነቅ የታሪክ ተቆርቋሪነት፣ የአለፈውን ትውልድ ገድል የሚያመላክት፣ ይህን ትውልድ ለማንነቱ ግንዛቤ የሚሰጡ መጸሕፍትን ወገን ያንብበው ብሎ በሚገባና በሚረዱት ቋንቋ ማቅረብና ማስነበብ ትልቅ ስጦታ ነው።ግደታቸውን የተወጡ፣ የትርጉም ጸሐፊዎች የታሪኩ ባለቤት፣ የወገን አክብሮትና ፍቅራቸውን በሚገባ የገለጹ የዚህ ትውልድ ግደታን ያከናወኑና እንድሁም ደግሞ የቀደምት ትውልድን መሰዋእትነት በሚገባ ያከበሩና ያወደሱ ሲሆን በቀጣይነቱንም ለዚህ ትውልድ በመቆርቆር ያቀረቡ ኢትዮጵያዊነትም በፅናት ይተገበር ዘንድ ታሪካችንን ተርጉመው ያላወቅነውን እንዲናውቅ የሚያስተምሩ መጸሕፍትን አቅርበውልናል።

ትውልድን ማስተማርና ማንነቱን ማስገንዘብ ፣በተገቢ ሁኔታ መቅረጽና የአገር ፍቅር ማሳየት የኅብረተስብ የታሪክ ዋና ክፍል ነው።እነዚህን መጸሐፍት ለኢትዮጵያ ሕዝብ በሚገባው ቋንቋ ተተርጉመው ለንባብ ለእኛ ስላደረሱ አንብበን መረዳትና በተግባር ሥራ ላይ ቀጣዩን ታሪክ መስራት የኛ ፈንታ ነው። እኔ የማላውቀውን እንዳውቅ ስለረዱኝና የኢትዮጵያን ታልቅነት ስላስገነዘቡኝ በድጋሜ ከልብ እያመስገንኩኝ እግዛብሔር ይባርካችሁ፣ የኢትዮጵያ አምላክ በታሪክ መዝገብ ያኑራችሁ በማለት እየተመኘሁ መጸሐፎቹ በማንኛውም ኢትዮጵያዊ እንድነበቡና ታሪካዊ ቅርስነታቸውም እንድከበርና እንድጠበቅ አደራ ጭምር አሳስባለሁ።

በነዚህ መጸሐፍት ውስጥ ብዙ የታሪካችን መልካምና የጥቂት ኅብረተስብ መጥፎ ጎኖች ተብራርተዋል፤ ኢትዮጵያዊነትንና ታሪክን በደንብ ማወቅ ፣ ማስተዋልና መረዳት እጅግ በጣም አስፈላጊና መሰረታዊ የአገርና የሕዝብ አውታር ነው። ኢትዮጵያን ብዙ የተፈታተኗት ጦርነት ፣ የወረራ ኃይሎች ተደጋግሞ

ተሞክሮል፣ ይሁን እንጂ የእኛ ቀደምት ኢትዮጵያዊ ትውድል በአገሩ ከፍተኛ ፍቅርና አክብሮት ሕይወቱን ለመስዋእትነት መሰረት አድርጎ ከውጭና ከውስጥ ከሃዲዎች ጭምር ተፋልም የጠበቃት ፣ የፈጠራትና ያቆያት አገር ናት።

በጉልህ እንደሚታውቀው ጣሊያን ከአንድም ሁለት ጊዜ የወረራ ሙከራዎች ሲያደርግ አገር ከሃዲ ባንዳዎች ለጠላት አጋር በመሆን ከፍተኛው በደል የፈጸሙብን፣ ለብዙ ስቃይና ዘረፍ፣ በአጭር ጊዜ የተገኙ ድሎች መስናከል ሆነው ያወኩንና የወጉን የዚያ አካባቢ የትግራይና ኤርትራ ከሃዲዎች ነበሩ። በአራት ወር ጊዜ ውስጥ ተጠናቆ ያለቀውን የኢትዮጵያ ጀግኖች ሞትን ሞተው በማይጨው ላይ ያገኙት ድል ለጣሊያን የሆነውና ወደ አምስት ዓመት የከፋ ትግል የተራዘመው በባንዳ መሪዎች ተደራጂተው በጣሊያን መሳሪያ በታጠቁ አገር በከዱ- በንዳዎች በራያና አዘቦ የትግራይ ክፍለ አገር ተወላጆች ከኃላ ተደብቀው በሸፍጥ በተደረገ ክህደት የሌብነት ውጊያ ነበር።

ከሃዲ ባንዳዎች ለጠላት አጋር ሆነው ብዙ አሳዛኝና የታሪክ ጥቁር ነጥቦችን አስቀምጠዋል። የጦር መሪ ጀግና ስመጥሩ አርበኞች የአድዋን ጦርነት የመሩና በድል አድራጊነት የታወቁትን የአጼ ምኒልክ የጦር አበጋዝን ራስ ሙሊጌታ በራያና አዘቦ ሽፍቶች በደፈጣ በተትኮስ ጥይት ከነልጃቸው በአሸንጌ ሐይቅ ተመትው ወድቅዋል። ድል እንድቀለበስ ተደርጓ፣ ብዙ ሺ- ኪሎ ሜትር ተጉዘው የመጡ ወታደሮች በከሃዲዎች ተገለዋል፣ ቆስለዋል ። የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች በባንድ እጅ ተመተው ወድቀዋል። አሳዛኝ ለዘለዓለም የማይሽር ቁስልና በማይረሳ ሃዘን ፀረ-ኢትዮጵያ ተግባሮች ተፈጽመዋል፣ ተመዝግበዋል።

ለጣሊያን ወራሪ ኃይል አጋር በመሆን በአገርና በወገን ላይ ሸፍቶ ከተለያየ ርቀት የኢትዮጵያ ክፍል ለአገር ዋስትና ሊረዳ፣ ሊዋጋና ለነፃነት የመጣውን ወታደር እየተደበቁ ከጠላት በፊት ሆነው ወጉቱ፣ መሳሪያውን ዘረፉት፣ ስንቁን ቀሙት፣ ዋሻውና መንገዱን ለጠላት ጠቆሙበት፣ ከጠላት ጋር ተባብረው ወጉት ፣ ገደሉት። ከዚህ ባሻገር ከሃዲ-ባንዳዎች የአካባቢ ኗሪውን ሕዝብ (ትግራይ፤ ራይና አዘቦ እንዱሁም የኤርትራው ባንዳ) ከኢትዮጵያ ውታደሮች ጋር እንዳይተባበር፣ እንዳይዋጋ በማስተባበር የጣሊያኑን ባንዲራ በማውለብለብ ወዶገብ ባንዳ አድርገውት በወንድም-እህቱ ላይ ዘመተ። አርበኛውን ብዙ ያስቸግሩና አውኮት ነበር። በስመ ጥሩው መሪ በአፄ ምኒልክ አምላክ ተማጽነው የለመኑትንና የገቡትን ቃል በማፍረስ በባንዳ ባህሪቸው በወገን ላይ ከኃላ ተደብቀው በመውጋት ከፍተኛ ሸፍጥና በደላ አካሂደዋል ። ከረዥም ጎዞ በኃ ተራርውን፣ አቅበት ቁልቁለቱን፣ጫካውና ደኑን፣ በረሃውን መንገድ አቋርጦ የመጣውን (አማራውን፣ አኦሮሞውን፣ ከንባታውን...ወዘተ.) በወድሞቹ ተዘምቶ፤ ገለውታል፣ ዘርፈውታል፣ የሚጠጣውን ውሃ በመርዝ በክለውታል።

የኢትዮጵያ አርበኞች ሽንፈትን የማይቀበሉ፣ ፍርሃትን የማያውቁ በቆራጥነት ክንዳቼውን አስተባብረውና አጠንክረው ከሃዲ-ባንዳውና ጠላትን አርበድብደው በማሸነፍ ድልን ተቀዳጅተው ኢትዮጵያን ነፃ አውጥተዋል። በዚያ የአምስት አመት የጦርነትና የረዥም ጉዞ ስቃይና እልቂት በኃላ የተገኘው ድል በአማራው፣ ከንባታው፣ አኦሮምው፣አፋሩ በጠቅላላው የሌላው ክፍል ሕዝብ የጋራ ለአገር ነፃነት ያልተቆጠበ ጥረትና ተጋድሎ በማድረግ ኢትዮጵያዊነትንና የአገሩ ባለቤትነትን አረጋግጧል።

ነግር ግን ባንዳዎች ከሃዲነታቸውን ሳያፍሩበት ክህደትን በማጠናከር ከድል በኃላም ለኢትዮጵያ አንገዛም፣ አንገብርም በማለት የመጀመሪያውን ወያኔ አቋቁመው በማመጽ በአገሪቱ ላይ ህውከት ፈጥረው ብዙ አስቸግረው እንደነበር የሚታወስ ነው። ይሁንና አስፈላጊው ቅጣትና ትምህርት ከተሰጣቸው በኃላ አደብ

ገዝተው እንደነበር በብዙ ታሪክ መጸሐፍቶች በዝርዝር የተጻፈ ነው። በዚህ ሁኔታ የሰሜኑ ክፍል ኅብረተሰብ ከሃዲ-ባንዳና አዋኪ የነፃነት እንቅፋት ለመሆኑ ግልጽና ቁልጭ ያለ ዛሬም እኛ ምስክር በምንሆንበት መልክ የምናዬው የነአቶ መለስ ዜናዊ ቡድን ወያኔ ከየትና እንደት እንደተፈጠረና የአገር አጥፊነት ተግባሩን እያየንነው።

በነዚህ ሁለት መጸሕፍት የትግሬው ራያና አዘቦ፣ አድዋው፣ ኤርትራው አካባቢ ከሃዲ-ባንዳነት፣ ፀረ-ኢትዮጵያዊነት ጥንትም የነበረና ያለ አስቸጋሪ የታሪካችን ሃቅ ታሪክ በትክክል የተቀመጠ ስለሆነ አንብበን መረዳትና በትግባር እንዲውል አስተዋፃኦ ማድረግ ለአገር ጠቃሚ አሰላለፍና የባለቤትነት ኃላፊነትና ግደታም ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ በተለይ ወጣቱ ጥልቅና የላቅ ኃልፊነት አለብህ። ኢትዮጵያን ይህ ትውልድ ነፃ ሊያወጣት ሊጠብቃትና ለመጭው ትውልድ ሊታደግ ግደታም ኃላፊነትም አለበት። የተዘጋጀ መሪ ድርጅት ባይምራ፣ ባይደራጅ፣ባያስታጥቅ ችላ ሳትል በራስህ ተነሳስተህ ተባብረህና አንድ ሆነህ በጽናት ቆርጠህ ለግብታዊ አመጽ መነሳትና አገርህን ከወያኔ ነፃ ማውጣ ይኖርብሃል። የወያኔ ሥር-ዓት የፀረ-ኢትዮጵያዊነት ፣ የዘረፋ፣ የአገር መሸጥ ፣የጥፋትና የወራሪነት ፀረ- ብሔራዊ ኢትዮጵያ ስለሆነ በነአቶ መለስ፣ አቶ ስብሃት ወይም የሌሎች ሞትና መጥፍት ብቻ ሳይሆን ጠቅላላ የዘረጉት የቋንቋ ክፍፍል ሥራዓታቸውና የውሸት ሕገ-መንግሥታቸው መደምሰስና መጥፍት እንድሁም በምትኩ ኢትዮጵያዊ ብሔራዊ መንግሥት መመስረት አስቸኳይና አንገብጋቢው ተግባር መሆን አለበት። ከዚህ ያነሰ ኢትዮጵያዊነት ሽንፈት፣ ደካማነት፣ የታሪክ እንከን ፤ የሚያሳፍርና ከንቱነት ይሆናል።

ምንጊዜም ኢትዮጵያ!
ለዘለዓለም ትኑር !

ሐምሌ28/2004